# የብሄረ ኣግኣዝያን ግስጋሴ፤ በምስራቅ አፍሪካ አዲሱ ክስተት

ሙሉማር ኪሮስ
mulumarkiros@gmail.com

ነገደ ኣግኣዝያን (ትግርኛ ተናጋሪ ህዝቦች) ተገደው ለሁለት የተከፈሉበት ጊዜ ድፍን 128 ዓመት ሞላው። እነዚህ ህዝቦች አብረው ዶግዓሊ፣ ጉራዕ፣ ኩፊት፣ ሰሓጢ፣ መተማ በጀግንነት ሲፋለሙ ውለው ነበር ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ የተለያዩት። ንጉስ ሚኒሊክ (በኋላ ዐፄ) የዐፄ ዮሃንስ መሰዋት (ቀኑ እ.አ.አ. ማርች 10፣ 1889 ነበር) የሰሙት ከሁለት ሳምንት በኋላ ማለትም እ.አ.አ. ማርች 24, 1989 ነበር። እሳቸውም የዐፄ ዮሃንስ መሰዋት በሰሙ በሁለተኛው ቀን (እ.አ.አ. ማርች 25/26 1889) ለ ለጣልያኑ ንጉስ ኢምቤርቶ ደብዳቤ ፅፈው ጣልያኖች በፍጥነት ከመረብ ወድያ ያለውን የኢትዮጵያ ክፍል እንዲቆጣጠር ፈቀዱ፤ ሳይዘገዩም (ከ 6 ቀን በኋላ) ማለትም እ.አ.አ. ሜይ 2፣ 1889 የውጫሌ ስምምነት ፈርመው (በዓንቀፅ 3 መሰረት) ነገደ አግአዝያኖችን ለሁለት እንዲከፈሉ ከጣልያኖች ጋር ወሰኑና ተገበሩት።

ዓፄ ዮሃንስ፣ ራስ አሉላ፣ ደጃዝማች ባህታ ሃጎስ፣ ራስ ሃጎስ፣ ወዘተ ከመረብ ወዲህም ወድያም የነበሩ ጀግኖች እረፍት በሌለው አኳኋን አንዱ ጠላት ሲሸነፍ ሌላው እየተተካ (ግበፅ፣ ቱርክ፣ ጣልያን፣ መሃዲስት) ለብዙ ዓመታት ሀገራቸውን ሲከላከሉ ከቆዩ በኋላ ማሃዲስቶች በጎንደር በኩል መጥተዋል ሲባል ከሰሜን ኤርትራ ጀምረው በፍጥነት ያሁሉ ኪሎሜትሮች ተጉዘው ከማሃዲስቶች ጋር በጀግንነት ተፋልመው ንጉሰ ነገስቱና ብዙ ጀግኖቻቸውን አጥተዋል። ይህ በድካማቸው ላይ የንጉሰ ነገስታቸው መሞት ተጨምሮ ከፍተኛ የሞራል ጉዳት በደረሰባቸው የሁለት ሳምንታት ጊዜ ውስጥ ጠላቶቻቸው ጊዜ ሳይሰጡና ካለ ምንም ምህረት አልሆነ ቦታ ላይ ገመሱዋቸው።

ነገደ ኣግኣዝያን ይህ ደባ ሁሌም እንደ አዲስ ያንገበግባቸዋል፤ ጥቃቱ ያበግናቸዋል። ባለፉት 20 ዓመታት ሁለቱም ህዝቦች አንፃራው ሰላምና ልማት ሲያገኙ ሲያብሰለስሉት የነበረ ስሜት ቢሆንም ዓምና በአማራ ክልል ውስጥ በትግራይ ህዝብ ላይ ከደረሰው እልቂት በኋላ ግን ግብታዊ በሆነ መልኩ አገርሽቶባቸዋል። በአሁኑ ሰዓት በየ ኢነተርኔት ካፌና የሞባይ ኮኔክሽኖች፤ በማህበራዊ ድህረ-ገፆችም ይሁን በነገደ ኣግኣዝያን ዌብ ሳይት የእንቅስቃሴው ዕድገት መከታተልና መወያየት የያንዳንዱ የትግራይና ኤርትራዊ ወጣት ሱስ ሆኗል ማለት ይቻላል። “ዮኒከ ኢትማስን ተስፍከ ዘውድቀ ይተንሳእ!” ብለዋል በጥንቱ ቋንቋቸው።

ነገደ አግኣዝያን ትርጋሜው አይበገሬው ነፃ አውጪ ብሄር ማለት ሲሆን ጀግንነታቸው ወደር የለሽና ግዛታቸውም ከምስራቅና ሰሜን ምስራቅ አፍሪቃ እስከ መካከለኛ ምስራቅ ይደርስ እነደነበር የታሪክ ድርሳኖች ያመላክታሉ። ቀን ሲጥል ግን ወር ባልሞላ (ዓፄ ዮሃንስ በሞቱ በ22 ቀናቸው) አብሮ የፈሰሰው ደማቸውን እንኳ ሳይደርቅ ለሁለት ተከፍለውና ተዳክመው ለድፍን 100 አመታት በድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ሲኖሩ ቆይተዋል።

ታሪክ እንደሚያስረዳው ነገደ ኣግአዝያን ከ 1980 ዓ.ዓ በፊት ጀምሮ ማንነታቸውን ለአራት ሺ ዓመታት ያክል ጠብቀው የኖሩ ህዝቦች ናቸው። ይህንን አንድነታቸውን ለመመለስ በተለያዩ ጊዜያት በተለይም በ1940ዎቹ፤ 1960ዎቹና እንዲሁም ባሁኑ ጊዜ በበርካታ ግለሰቦችና ቡድኖች ጥረቶች ተደርጓል፤ በመደረግ ላይም ይገኛሉ። ከነዚህ ቡድኖች ጥረት ውስጥም ዋነኞቹ፡-

(1) በቀዳማይ ወያኔ በ 1940ዎቹ በትግራይ በኩል ተደርጎ የነበረው ጥረት፤ (2) በኢጣሊያና በእንግሊዞች በኩል በተለያዩ ጊዜያት የትግራይና የኤርትራ ተወላጆችን በማካተት የተደረጉ ጥረቶች፤ (3) በኤርትራ ውስጥ በ 1940-60ዎቹ ሲንቀሳቀስ የነበረው የሊበራል ዲሞክራቲክ ፓርቲ እንዲሁም (4) በአሁኑ ጊዜ በተለይም እ.አ.አ. ከ2000 ዓ.ም እየተካሄዱ ያሉት የዲሞክራስያዊት ሪፐብሊክ ሃገረ አግአዚያን ምስረታ ይገኙበታል። በነዚህ 128 ዓመታት ውስጥም አንዴ ቀዝቀዝ አንዴ ጋል እያለ የቆየ ሲሆን ከሁሉም ጊዜያት ይልቅ እንደ አሁኑ በሁለቱም የትግርኛ ተናጋሪ ህዝቦች የጋለ ስሜት የፈጠረበት ጊዜ አልነበረም።

## ሀ. የዲሞክራሲ ሪፐብሊክ ብሔረ አግአዚያን (ዓባይ ኤርትራ) አመሰራረትና ዓላማ

እላይ እንደተገለፀው ብሄረ አግአዚያን ወይም ዓባይ ኤርትራ (ትግራይ ትግርኚ) በተለያዩ ጊዝያትና ቡዱኖች እየተጀመረ ሲከስም የኖረ የነገደ አግአዝያን አንድነትና የሉአላዊት ሃገር መመስረት ፅንሰ ሃሳብ ነው። በውራይና መፅሄት ጥር 2009 ዓ.ም 35ኛው ዕትም ውስጥ አቶ ጌታቸው አረጋዊ የተባሉ ፀሃፊ ፕሮፌሰር ተስፋፅዮን እና ፕሮፌሰር አለምሰገድ አባይን ጠቅሰው እንደፃፉት ዓባይ ኤርትራን (ወይም ትግራይ ትግርኚ) የመመስረት ፅንሰ ሃሳብ የመጣው በማዕከላይ መንግስት በደል እየደረሰብን ነው ብለው በተነሱ የትግራይ ተወላጆች ሆኖ የኤርትራ ትግርኛ ተናጋሪዎችም ደግፈውት እንደነበረ፤ በኋላም መጀመሪያ በኢጣሊያን መንግስት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የኮሎኒ ፅ/ቤት በኩል ተቀባይነት ያገኘ ሃሳብ ነበር ብሏል።

እንግሊዝ ኤርትራን በምታስተዳድርበት አጭር ጊዜ ውስጥም እንግሊዞቹ ሃሳቡን አንስተው ከኢጣሊያን መንግስት እንደተመካከሩበት ይገልፃሉ።

የዚህ ፅንሰ ሃሳብ አነሳሱ መለያየት የማይቻልና የማይገባው አንድ የሆነን ህዝብ በአንድ አስተዳደር ወይም አገር አደራጅቶ የጋራ ቋንቋቸው፤ ባህላቸው፤ታሪካቸውና ማንነታቸው የማበልፀግ የታሪክና የማንነት ኃላፊነት ይዞ የተነሳ ነው። በአሁኑ ጊዜ በመስፋፋት ላይ ያለው በኤርትራዊው አቶ ተስፋፅዮን የተቋቋመው የብሄረ አግአዚያን ምስረታ በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ ስሞች የነበሩት ሲሆን አሁን በሚታወቅበት ስም የዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሃገረ አግአዚያን በሚል ለመጠራት በቅቷል። ይህ በኤርትራ በኩል የተጀመረውና ሞቅ ቀዝቀዝ እያለ የቆየው አንቅስቃሴ በአሁኑ ሰዓት በሁለቱም በኩል ካሉት ነገደ አግአዚያን በሰፋት ተቀባይነት በማግኘት ላይ ይገኛል። በተለይም በውጭ በሚኖሩ የዚሁ ብሄር አባላት በስፋት ድርጅቱ ውስጥ እየተቀላቀሉ በተለያዩ የአውሮፓ አገራትና ከተሞች ፅ/ቤት እያቋቋሙ በፍጥነት እየተስፋፉ ይገኛሉ።

## ለ. በትግራይና በኤርትራ በኩል የሃረ አግአዚያን እንቅስቃሴ ለማስፋፋት ያሉ ምቹ ሁኔታዎች

ሁለቱም ህዝቦች አስከፊ በሆነ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር ውስጥ ወድቀው ያን ለመቀየር ሲሊ ለመናገርም ይሁን ለመፃፍ የሚከብድ ከፍተኛ መስዋእትነት ከፍለው አንፀባራቂ ድል አስመዝግቧል። ሆኖም በኤርትራ በኩል ያለው አምባገነኑ የኢሳያስ መንግስት በህዝቡ መስዋእትነት የተገኘን ሰላም ለልማትና ብልፅግና ከማዋል ይልቅ ለጠባብ ዓላማው ፍላጎት ለማሳካት ብቻ አውሎታል፤ ሃገሪቷና ህዝቦቿም ለድህነት፣ ስደትና ሰቆቃ ዳርጓታል። ይህንን ሁኔታ ለመሸሽ የኤርትራ እህትና ወንድም ህዝብ በቅርቡ ትቶት ያለፈው የጦርነት ጠባሳ ሳያስጋቸው ወደ ትግራይ በመሻገር በተለያዩ የስድተኞች ጣቢያ ሲገቡ የትግራይ ህዝብ በደስታ ተቀብሎ አስተናግዷቸዋል። ከዚህም ባለፈ ወገኖቹ በምርጫቸው በተለያዩ የትግራይ ከተሞች ከህዝቡ ጋር እንዲቀላቀሉ በተደረገው ጥረት በUNHCR (ዩኤንኤችሲአር) እና የትግራይ መንግስት ድጋፍ የገንዘብና የመስሪያ ቦታ እየተሰጣቸው (የማይናቅ ቁጥር ያለው ኤርትራውያን ተማሪዎችም በተለያዩ ዩኒቨርሲቲች ትምህርታቸውን እየተከታተሉ) ወንድም ከሆነው የትግራይ ህዝብ አብረው ሲኖሩ የህዝቡን ፍቅርና ስሜት አይተው ረክተውበታል። ገሚሱም ከየ ስደተኛ ጣቢያው በቀጥታ ወደ አውሮፓና አሜሪካ ሲሸኝ የትግራይን ህዝብ ፍቅር ሰንቋል።

በትግራይ በኩል ሲታይም ባለፉት አንድ ሺ አመታት (ከ 11ኛው ክ/ዘመን ጀምሮ) በነበረው ተከታታይ የስልጣን ሽኩቻ በአንድ ወቅት የነበረን አንፃራዊ ሰላምና ልማት ከትንሽ አመታት ቆይታ በኋላ በሚደረገው የስልጣን መነጣጠቅ ጦርነት ምክንያት የነበረው እንዳልነበረ እየወደመ ድምር ውጤቱም የኋሊት ሽምጥ የተጓዙበት ጊዜ ነበር። ያ ሁሉ የዐዌዎቹ የስልጣን መነጣጠቅና ጦርነት አልፎ አሁን ህዝቦች በጋራና በእኩልነት መተዳደር ቢጀምሩም የድሮ ናፋቂዎች፣ ታሪካዊ የሃገሪቱ ጠላቶች፣ ጠባቦችና ፅንፈኞች በተደጋጋሚ በጋራ አቅደውና አቅማቸውን አሰባስበው በቀኝ በግራ እያሉ ሰላሙን አሳጥተውታል።

የትግራይ ህዝብ አሁን በሃገሪቱ ከተረጋገጠው ሰላምና እኩልነት ያነሰ ለመቀበል ዝግጁ አይደለም። በመከባበር ከሚመሰረት አንድነት ውጪ ለመኖርም ፍላጎት የለውም። በመሆኑም አሁን ያለው ሳይሆን ቢቀር በየዘመናቱ ሲከፍለው እንደነበረው ተጨማሪ መስዋዕትነት እየከፈለ መቀጠልን ምርጫው አይደለም። ባለፉት 25 ዓመታት እንደታዩት በማንም ይሁን በየትኛም አካባቢ የሚነሳ የመንግስትና የስልጣን ይገባኛል ተቃውሞ ሄዶ ሄዶ አልሳካ ሲላቸው ተቀዋሚዎቹ የንዴትና የእልህ ማብረጃቸው ንፁሁና ሰላማዊ የትግራይ ህዝብ አድርገዉት ቆይተዋል። ይህ አይነቱ መረን የለቀቀ ቦዘኔነት ማቆምያው ቅርብ ነው እንዳይባል በአሁን ወቅት ያለው አጠቃላይ የሃገሪቱ ዝቅተኛ ንቃተ ህሊና እና ጠላቶቹ ካላቸው ድምር አቅም ሲታይ መጪው ጊዜም ቀላል እንዳልሆነ ይታወቃል።

አንድ በሁሉም ተቃዋሚ ሃይሎች ዘንድ የሚቀነቀንና ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም በቅርቡ በግልፅ ቋንቋ እንደነገሩን "የትግራይ ህዝብ ዛሬ ነገ ሳይል ሌላው የኢትዮጵያ ወገኑ (የተቃዋሚ ሃይሎችን ማለታቸውን ነው) ደግፎ ህወሓትን የማይወጋ ከሆነ በአራት ማእዘናት በኩል ያሉት ጠላቶቹ <የመስቀል ገንፎ> ያረጉታል ብሏል"። በመሆኑም "የኛ ፕ/ር" እንዳስገነዘቡን የትግራይ ህዝብ እሳቸው የጠሉትን ካልጠላ <እንደ መስቀል ገንፎ> ተቃዋሚዎች ከበው ቦጫጭቀው ይበሉታል። በነሱ የፖለቲካ መዝገበ ቃላት <ጠላቴን ያልጠላ፤ ያው ጠላቴ ነው> የሚል ነው። አበስኩ ገበርኩ!!

የትግራይ ወጣቶች በዚሁ ክህደት ተፈፅሞብናል ብለው በሚያስቡበት ወቅት ነው ከመረብ ወድያ ያሉት እህትና ወንድም ኣግኣዝያኖች የፍቅርና የአንድነት ዜማ እያስተጋቡ የሚገኙት። <ሃበ ኣግአዝያን ከመ ይብራህ ደመራሁ ለኩሉ ዓለም!!>

አግአዚያኖቹ ለዘመናት አንድ ዘር ሆነው ሳለ በጠላቶቻቸው ሴራ በመሃከላቸው ላይ የተሰመረባቸውን የመረብ አጥር ማየትም ሆነ መስማት እንደማይፈልጉ በቅርቡ በሚያሳዩዋቸው እንቅስቃሴዎች ገሃድ በማድረግ ላይ ናቸው። በተጨማሪም ከአሁን ወድያ በተናጠል መኖሩና የጋራ ጠላትን በየግላቸው መታገሉ ጠቃሚ ካለመሆኑም በላይ ብዙም ሳይርቁ ማንነታቸውንና የማንነታቸው መለያ የሆነው የጀግንነት ታሪካቸው፣ ቋንቋቸውና ባህላቸው እንደሚጠፋ ተገንዝበውታል።

ጥያቄው እንዴት፣ የትና በምን ያህል ፍጥነት አንድ ይሆናሉ የሚሉት ናቸው። ይህም በዚህች ፀሃፊ እምነት በዋናነት በኢትዮጵያ ያለውን የሰላምና የዲሞክራሲ ግንባታ ሁኔታ ይወስነዋል የሚል ነው። ይህ ማለትም በኢትዮጵያ ውስጥ ባለፉት 25 ዓመታት የታዩት አንፃራዊ የሰላም፣ የዲሞካራሲ ትግልና ልማት የሚቀጥሉ ከሆነ የኤርትራ ነገደ አግአዚያን ከመረብ ወዲህ ካለው እህትና ወንድም አግአዚያኖች የመሳብና ሁለቱም በኢትዩጵያ ውስጥ የሚተዳደሩበት ዕድል ሰፊ ይሆናል።

ይህ ሳይሆን ቀርቶ በኢትዮጵያ ውስጥ አሁን ያለው የጥበትና የትምክህት ሀይሎች በተለይም በጎረቤት ክልል የመሸገው የትምክህት አንጃ አቅሙ እያደራጀና እየተንሰራፋ በትግራይ ህዝብ ላይ የሚስከትለው ጥፋት የሚቀጥልበት ከሆነ ግን አጭር በሚባል ጊዜ ውስጥ የሀገረ አግአዚያን ነፃነት እውን ይሆናል።

ህዝቦቹ የሚመርጡት አማራጭ የማይፈለገውንና ሁተኛው ከሆነ የቀረችው ኢትዮጵያ ዕጣ ፋንታ እንዴት ይቀጥል ይሆን? የውስጥ አርበኛውና የትምክህት ሃይሉ ገኖ የኦሮሞ ህዝቦች እንደገና ወደ ዳግም ባርነት ይከታቸው ይሆን? አሁን በሚታየው አሰላለፍ የጉራጌ አንዳንድ ኤሊቶችና ባለሃብቶች ከትምክህት ሃይሉ ጋር በጥገኝነት ተሰልፈዋል። እናም በቀረችው ኢትዮጵያ የትምክህት ሃይሉ አሸንፎ በኦሮሞ ምድር ላይ ሃብት አካብተውና ተንሰራፍተው የሚኖሩበት ዕድል ሰፊ ይሆን? የኢትዮጵያ ሶማሌ ወንድሞቻችንስ ቆይታ ምን ያክል ጊዜ ይሆን?

**ቸር እንሰንብት!**

**<u>ማሳሰብያ፥</u>**
የዚህ ፅሁፍ ዓላማ በስፋት እየታየ ያለውን ክስተትና ሂደት መዳሰስ ብቻ ነው። ወጣቶቹ ይበል በሚያስብል ሁኔታ በተለያዩ የህትመት ውጤቶች (በተለይም በዋና ዋና ከተሞቻችን)፣ በማህበራዊ ድረገፆች እና ዌብ ሳይቶች እየተወያዩበት ይገኛል። ከነዚህ ነጥቦች ውስጥም በህዝቡ ዘንድ እየተስፋፋ ያለው የእንቅስቃሴው ስርጭት ፍጥነትና አድማስ፣ የዚህ ዓይነት ንቅናቄ ጥቅሙ፣ የመተግበር እድሉ (implementability)፣ ሊያስከትል የሚችለው ሁሉም ዓይነት ጉዳቶችና መፍትሄዎቻቸው፣ ከሌሎች ብሄሮች ስለተጋቡና ከክልላቸው ውጪ ንብረት ስላፈሩ የብሄሩ ተወላጆች መፃኢ ዕድል፣ የሁለቱም መሪ ድርጅቶች (ህግደፍና ህወሓት) የህዝቡን ስሜት በምን መልኩ ይቀበሉታል?፣ ወዘተ የሚሉ ይገኙበታል። የዚህ ፅሁፍ ዓላማም ይኸው ነው፤ መነጋገር፣ መወያየት።